# ሞረሽ ለአማራው

አገሬ ከስዊድን
20120401

አባቶች ተጣሩ ፤ ሞረሽ ሞረሽ ብለው
አንተም ልጅ ነህና ፤ ምላሽ ስጥ ለጥሪው
ሞረሽ ብለህ ቀጥል ፤ ጥሪው ለሁሉም ነው ።

ጥንስስ ሲጠነሰስ ፤ ኢትዮጵያ እንድትጠፋ
ታሪክን ማቆሸሽ ፤ በግላጭ በይፋ
አማራን መኮነን ፤ አንገት እንዲደፋ
ትውልድ በመጨረስ ፤ ወያኔ እንዲስፋፋ
በአይን እያየን ነው ፤ አማራ ሲገፋ ።

መጠበቅ ያሰበ ፤ ኢትዮጵያን ማትረፍ
አማራን ሳያድን ፤ ሲል እንገፍ እንገፍ
በያደባባዩ ፤ በጠላት እጅ ወድቆ
በፍርሀት ተውጦ ፤ ባልሰራው ተሳቆ
እተዳደር ብሎ ፤ ከአራጁ እየዋለ
ተናቀ ተጠላ ፤ ጡት ቆራጭ ተባለ ።

ቢቸግር ነው እንጅ ፤ ቢጨንቅ አማራ
ምን ትብብር ሊኖር ፤ ከገዳዩ ጋራ
መብቱ ሳይከበር ፤ ውነት ሳይወራ
እነኳንስ አገሩን ፤ ልጁን ሳያተርፍ
ገረፉት በቋንቋው ፤ ገደሉት በግፍ ።

ሞረሽን የሰማ ፤ ያደጋውን ጥሪ
እሱም ሞረሽ ብሎ ፤ ይጥራ ተባባሪ
ለወገኑ ይደረስ ፤ ይሁን ተቆርቋሪ ።

ተጋዘ ተገፋ ፤ አማራ ታረደ
ከነነፍሱ ቆሞ ፤ ገደል ተሰደደ
በዘረኛው ሁሉ ፤ እጅግ ተዋረደ ።

አማራ ታመሰ ፤ መከራ ወርዶበት
ነፍጠኛ ተብሎ ፤ ጥርስ ተነክሶብት
የጥላቸውን መርዝ ፤ ሲነሰሰንሱብት
በሽፍጥ ተነዝቶ ፤ ወንጀሉ በሀሰት
ታግሶ ቢያሳልፍ ፤ ሽንታም ተሰኘበት ።

መከበር ሲገባው ፤ አገር በማልማቱ
መደነቅ ሲገባው ፤ ሲቆም ለአንድነቱ
ዘረኝነት ይቅር ፤ ብሎ በማለቱ
ምነው እንደወንጀል ፤ አንገቱን መድፋቱ
ተመሳስሎ ማደር ፤ ምንድን ነው ጥፋቱ ።

በአባቶቻችን ደም ፤ አገር ተቀምራ
ክብሯ ተጠብቆ ፤ ሶስት ሺ አመት ኖራ
መመስገን ሲገባው ፤ ባለፈው ሊኮራ
ሁሌ ሲኮንኑት ፤ ባልዋለበት ስራ
ቅስሙን ሰባብረውት ፤ ጠላት አንሰራራ ።

አንገትን መድፋቱ ፤ ካልጠበቀ አገር
ባእድ ከወረሰው ፤ የኢትዮጵያን ምድር
ሞትና ስደቱ ፤ ለእሱ ሆኖ ግብር
ቆሞ ማየት ይብቃ ፤ ወገን ሲመተር ።

ተነሱ እንነሳ ፤ ወገን አንገት ደፍቷል
ኢትዮጵያ እናታችን ፤ ልጅ ያስፈልጋታል
ራስ መከላከል ፤ አደጋን ይገታል ።

ተከፋፍሎ መቆም ፤ መለማመጥ ትቶ
አማራን ማሳቀቅ ፤ ማሸመቀቅ ቀርቶ
ውነቱ ተነግሮ ፤ ወነቱ ተወርቶ
ወገንን ለማዳን ፤ ታጥቆ ተደራጅቶ
እንደ ጥንት አባቶች ፤ ራስን ሰውቶ
ማየትን እንሻ ፤ ሰቆቃው አብቅቶ ።

EthioLion.Com